# ወቅቱ የረቀቀ ዲፕሎማሲን ይጠይቃል

ነሐሴ 13 ቀን 2000 ዓ.ም. SUNDAY, 20 JULY 2008

ከአናሎግ ወደ ዲጂታል እየተለወጡ ያሉት ቴፕ፣ ካሜራና ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎች ብቻ አይደሉም። ዲፕሎማሲውም ረቀቅ እያለ "ከአናሎግ" ወደ "ዲጂታል" እየተለወጠ ነው።

ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲው ራሱ አሜሪካና ኢራን አይነጋገሩም ሲባል ይቆይና ወዲያው እየተነጋገሩ መሆኑ ዜና ይሰማል። ከሶሪያ ጋር እሳትና ጭድ ናቸው ይባልና የአሜሪካ ባለሥልጣን ሶሪያን ሲጎበኝ ይታያል። እስራኤል ሂዙቦላን ካላጠፋሁ ሞቼ እገኛለሁ፤ ሂዙቦላም እስራኤልን ካላጠፋሁ ሞቼ እገኛለሁ ሲሉ ቆይተው እስረኛ ሲለዋወጡ ይታያሉ። ዲፕሎማሲው ረቀቅ እያለ መጥቷል።

ለእኛስ ይህ ረቀቅ ያለ የወቅቱ ዲፕሎማሲ አይመለከተንም? ወይስ አናሎጉ በቂያችን ነው? የአገራችን ዲፕሎማሲ ወደ ላቀ ደረጃ ከፍ ሊልና ረቀቅ ያለ እንዲሆን ወቅቱ ይጠይቃል። በአስቸኳይ" የአጎራባች አገሮችና የእኛን ሁኔታ ሲታይ ረቀቅ ባለ ዲፕሎማሲ ልንፈታቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ እንገነዘባለን።

የዲፕሎማሲ አስፈላጊነቱ ከኤርትራ ጋር ያለው ችግር ለመፍታት ከፕሬዚዳንት ኢሳይያስ ጋር ግንኙነትና ሰላም ለመፍጠር አይደለም። ሆን ተብሎ ሃላፊነት በጎደለው ሁኔታ፣ የሚደረግ የአምባገነኖች እቅንቅስቃሴ ስለሆነ ተመክሮና ተዘክሮም የሚታረም መንግሥት በኤርትራ በኩል ያለ አይመስለንም። መታገስ ቢያስፈልግም እንቅስቃሴያቸው ለራሳቸው የሚጎዳ መሆኑን ማሳየትም ያስፈልጋል።

ከኤርትራ ጋር ባለው ግንኙነት ረቀቅ ያለ ዲፕሎማሲ የሚያስፈልገው ሕዝቡ ጉዳዩን እንዲገነዘበው ለማድረግና ዴሞክራሲያዊ የኤርትራ ሃይሎች እንዲጠናከሩና ፀረ ኢትዮጵያ የሆነ ሃይል ፀረ ኤርትራም መሆኑን በተገቢ መንገድ እንዲገነዘቡ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከዚሁ በተጨማሪ ደግሞ የዓለም ሕዝብ፣ የተባበሩት መንግሥታትና የአፍሪካ ሕብረት፣ ከኤርትራ ጋር ባለው ግንኙነት፣ ኢትዮጵያ ሰላም ወዳድ መሆንዋንና ለሂግ ውሳኔ ተገቢ ትኩረት እንዲሰጥ ማድረግ ይኖርበታል።

ሰላማዊና ዲፕሎማሲያዊ በሆነ መንገድ የኤርትራና የኢትዮጵያ ሕዝብ በኢኮኖሚ ትስስር ተጠቃሚ ሲሆን አሰብ ወደብ ለኤርትራ ገቢ የሚያስገኘው ለኢትዮጵያም የወደብ አገልግሎት ሲሰጥ እንጂ ቢዘጋና ሳር ቢበቅልበት ማንም ተጠቃሚ እንደማይሆን ማስገንዘብ ነው።

ከሱዳን ጋር ያለው ሁኔታ ረቀቅ ባለ ዴሞክራሲያዊ መንገድ መያዝ አለበት። ኢትዮጵያ ከሱዳን ጋር በጥሩ ወዳጅነት መኖር የምትችል አገር ናት። እስካሁንም ኖራለች። የተለያዩ ችግሮች ተፈጥረው መቃቃርን ሲያስከትሉ በቀላሉ ሲፈቱ ቆይተዋል።

ፕሬዚዳንት ሙባረክን ለመግደል ሙከራ ያደረጉት አሸባሪዎች ከሱዳን ጋር ይያያዛሉ ተብሎ መቃቃር ቢፈጠርም በበሰለ ዲፕሎማሲ ችግሩ ሊፈታ ችሏል። ነገር ግን የተወሰነ

መጋጨት ድንበር ላይ አጋጠመ ሲባል ነገሩን ማጦዝና ሊፈታ እንደማይቻል አድርጎ “አቧራ ማሳነሳት” አያስፈልግም። ረቀቅ ያለ ዲፕሎማሲ ያስፈልጋል ስንልም ይህን ማለታችን ነው። የሰከነ፣ ችግሮችን ጠልቆ የሚያይ ዲፕሎማሲ ማለታችን ነው።

በተለይ በአሁኑ ጊዜ በርካታ ኢትዮጵያውያን በሱዳን ይንቀሳቀሳሉ። በተለያዩ የሥራ መስኮችም ተሰማርተዋል።

የሱዳን ባለሃብቶች ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት እያካሄዱ ነው። በነዳጅ አምራችነቷም ቅርብ በመሆኗ ጥሩ ወዳጅነት ይጠቅመናል እንጂ የሚጎዳን አይደለም።

አለም አቀፍ ሁኔታዎችና ብሄራዊ ጥቅማችንን አመዛዝኖ፣ በሰላም በረቀቀ መንገድ ግንኙነቱን መጠበቅ እንጂ ማባባስ ጠቃሚ አይደለም።

በአሁኑ ጊዜ የሻዕቢያ መረብን የሱዳን አንዳንድ ተንኮለኞች ኢትዮጵያ ላይ ለመፈጸም መተናኮል ቢጀምሩም ተጋፋችሁን ብለን ወደ “ይለያል ዘንድሮ” እንዳንገባ መጠንቀቅ አለብን።

ከጅቡቲ ጋር እጅግ ጠቃሚ ግንኙነቶች ነበሩን፣ አሉን፣ ለወደፊትም ሊኖረን ይገባል። እኛም እነሱም አንድ አገር፣ አንድ ሕዝብ አድርገን ራሳችንን የምንቆጥር ነን። የጅቢቲ ኢንቨስተሮች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ብቻ ሳይሆን ጅቡቲያውያን በኢትዮጵያ እንደሚኖሩ ቢቆጥሩም ምንም ስህተት የለበትም።

በአሁኑ ጊዜ በጅቡቲ የሚገኙ የወደብ አስተዳዳሪዎች በኢትዮጵያ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ለማድረግ ዝግጅት ላይ ናቸው። የምድር ባቡርና የነዳጅ ቧንቧ ለመዘርጋት ወስነዋል። እንደዚሁ ዓይነት ዓበይት የጋራ ጉዳዮች እያሉ፣ በተገልጋይ ላይ ዋጋ ተጨመረ፣ ጊዜ አጠረ፣ እየተባለ ግንኙነት እንዳይበላሽ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። በበሳልና ረቀቅ ባለ ዲፕሎማሲ ግንኙነቱ መዝለቅ አለበት።

ረቀቅ ያለ ዲፕሎማሲ እንዲኖር ስንፈልግ የሰው ኃይል ያስፈልገናል። እንዲህ አይነት ዲፕሎማቶች ካሉን መልካም፣ ከሌሉን ግን መቅጠርና ማሰልጠን ይኖርበታል። በድሮው መንገድ መሄድ አያዋጣም። ወቅቱ ረቀቅ ያለ ዲፕሎማሲ በአስቸኳይ እየጠየቀን ነውና”